# ሺጌሎሲስ (SHIGELLOSIS) 10/31/2023

## ፋይረሱ/ኢንፌክሽኑ ምንድን ነው?

ሺጌሎሲስ (Shigellosis) *ሸጌላ (Shigella)* ተብሎ በሚጠራ ባክቴሪያ ምክንያት የሚመጣ ኢንፌክሽን ነው። ሸጌላ (Shigella) የተለመደ የተቅማጥ መንስኤ ነው።

## ማንን ይይዛል?

ማንም ሰው በሺጌሎሲስ (Shigellosis) ሊያዝ ይችላል፣ ሆኖም እጅግ በአብዛኛው የሚያዙት የሚከተሉት ናቸው፡

- ዕድሜያቸው ከ5 ዓመት በታች የሆኑ ህጻናት
- በህጻናት እንክብካቤ ማዕከላት ውስጥ ያሉ ህጻናት
- ደካማ ንጽህና እና ጤናማ ያልሆነ ምግብ እና ውሃ ወዳለባቸው ቦታዎች የሚጓዙ ሰዎች
- መኖሪያ ቤት አልባ የሆኑ ሰዎች
- ከወንዶች ጋር የግብረ ሥጋ ግንኙነት የሚፈጽሙ ወንዶች

## ቫይረሱ እንዴት ይዛመታል?

አንድ ሰው በሺጌሎሲስ (Shigellosis) ከተያዘ ሰው ወይም እንስሳ ሰገራ (አይነ ምድር) ላይ የሚነሱ ጥቃቅን ብናኞች በድንገት ወደ አፉ ውስጥ ሲገቡና በሺጌሎሲስ (Shigellosis) ሊያዝ ይችላል።

ሺጌሎሲስ (Shigellosis) በተለይም የሚከተሉት ባሉባቸው ቦታዎች በቀላሉ ሊዛመት ይችላል:

- ንጽህናቸው ደካማ የሆነ
- ሰዎች ተፋፍገው የሚኖሩባቸው
- የተበከለ ምግብ ወይም ውሀ ያለባቸው

አንድ ሰው በሚከተለው ምክንያት ሊታመም ይችላል:

- በቫይረሱ ከተያዘ ሰው ጋር በቀጥታ በመነካካት። ለምሳሌ: የታመመ ሰው በመንከባከብ ወይም ዳይፐሩን በመቀየር።
- የተበከለ ምግብ ወይም መጠጦችን በመብላት/በመጠጣት
- የተበከሉ እቃዎችን ነክቶ ከዚያም እጆችን ሳይታጠቡ አፍ ውስጥ መክተት
- ንፁህ ያልሆነ ወይም ደህንነቱ ያልተጠበቀ ውሃ እንደ ሰዎች የሚዋኙባቸው ኩሬዎች ወይም ሀይቆች ካሉ ምንጮች በመጠጣት።
- በግብረ ሥጋ ግንኙነት ወቅት ከሰገራ ጋር በመገናኘት

## ምልክቶች ምን ምንድን ናቸው?

- ከመለስተኛ እስከ ከባድ ተቅማጥ፣ አንዳንድ ጊዜ የደም ወይም መግል ምልክቶች የቀላቀለ።
- ትኩሳት
- ማቅለሽለሽ እና ማስመለስ
- አንዳንድ ሰዎች ምንም ምልክቶች አይታዩባቸውም።

ምልክቶቹ በአብዛኛው ለባክቴሪያው ከመጋለጥ በኋላ ካሉት ከ1–3 ቀናት ውስጥ የሚጀምሩ ሲሆን በአንድ ሳምንት ያክል ጊዜ ውስጥ ይጠፋሉ።

## የሚመረመረው እንዴት ነው?

የላብራቶሪ ምርመራዎች ሺጌላ /Shigella/ን በሰገራ ውስጥ ሊያገኙ ይችላሉ።

## ህክምናው ምንድን ነው?

ብዙ ሰዎች ለመዳን መድሃኒት አያስፈልጋቸውም። ሰዎች የሰውነት ውስጥ ፈሳሻቸውን ለመጠበቅ ፈሳሽ መጠጣት አለባቸው። ከባድ ህመም ያለባቸው ሰዎች አንቲባዮቲክስ ሊያስፈልጋቸው ይችላል። አንድ ሰው አንቲባዮቲክስ የሚያስፈልገው ስለመሆኑ የጤና እንክብካቤ አቅራቢ ይወስናል።

ከቨርጂንያ ጤና መምሪያ Shigellosis ኤፒዲሚዮሎጂ የመረጃ ቅጽ ተሻሽሎ የተወሰደ (መስከረም 2018)
https://www.vdh.virginia.gov/epidemiology/epidemiology-fact-sheets/shigellosis

**ARLINGTON VIRGINIA** Public Health

# ሺጌሎሲስ (SHIGELLOSIS) 10/31/2023

## እንዴት መከላከል ይቻላል?

- በተለይም በሚከተሉት ሁኔታዎች እጆችን በተደጋጋሚ በሳሙናና ውሀ ቢያንስ ለ20 ሴኮንዶች መታጠብ፡
    - ሽንት ቤት ከመጠቀም ወይም ዳይፐር ከመቀየር በኋላ
    - ምግብ ከማዘጋጀት እና ከመመገብ በፊት
    - ከግብረ ስጋ ግንኙነት በፊት እና በኋላ
- ወይም አደገኛ ሊሆን የሚችል ውሃ አይጠጡ (ለምሳሌ፣ ከኩሬ፣ ከሐይቆች ወይም ከመዋኛ ገንዳዎች የሚወጣ ውሃ)
- የግብረ ስጋ ግንኙነት ለማድረግ ተቅማጡ ከቆመልዎ በኋላ ቢያንስ 2 ሳምንታት ይጠብቁ።
- ዓለም አቀፍ ጉዞ የሚያደርጉ ከሆነ ደህንነቱ የተጠበቀ አቀማመጥ እና የመጠጣት ልማዶችን ይከተሉ

## አንድ ሰው ቫይረሱን የሚያስተላልፈው ለምን ያክል ጊዜ ነው?

ሰዎች ምልክቶቻቸው ካቆሙ በኋላ እስከ 2 ሳምንታት ድረስ ሺጌሊዮሲስ /shigellosis/ን ሊያስተላልፉ ይችላሉ።

## አንድ ሰው ምን ያክል ጊዜ በቤት ውስጥ መሆን አለበት?

ተቅማጥ የያዘው ሰው ተቅማጡ እስኪቆምለት ድረስ በቤት ውስጥ መቆየት አለበት። የሚከተሉትን ጨምሮ የተወሰኑ ሰዎች መቼ ወደ ስራ ወይም ወደ ትምህርት ቤት እንደሚመለሱ በተመለከተ የጤና መምሪያን ማናገር አለባቸው:

- የምግብ ተቆጣጣሪዎች
- የጤና እንክብካቤ ሰራተኞች
- የህጻናት እንክብካቤ ሰራተኞች
- የህጻናት እንክብካቤ የሚከታተሉ ህጻናት

አንዳንድ ሰዎች በሰገራቸው ውስጥ ምንም ባክቴሪያ እስከማይኖር ድረስ ወደ ሥራ ወይም ወደ ሕጻናት እንክብካቤ መሄድ አይችሉም።

## ተጨማሪ መረጃ ማግኘት የምችለው እንዴት ነው?

- ስለ ሺጌሎሲስ (Shigellosis) ለተመለከቱ ጉዳዮች የጤና እንክብካቤ አቅራቢዎን ያነጋግሩ።
- ስለ ምግብ ወለድ ህመም ለተመለከቱ ጥያቄዎች የአርሊንግተን ካውንቲ የማህበረሰብ ጤና የተላላፊ በሽታ ፕሮግራም ድረገጽን በ (https://www.arlingtonva.us/Government/Programs/Health/Public-Health/Communicable-Disease-Programs) ይጎብኙ።
- የምግብ ወለድ ህመምን ሪፖርት ለማድረግ የMy Meal Detective ድረገጽን በ (https://redcap.vdh.virginia.gov/redcap/surveys/?s=PJACE4A4EY) ይጎብኙ።
- ስለ ሸጌላ (*Shigella*) በተመለከተ ተጨማሪ መረጃ ለማግኘት የCDCን ድረገጽ በ(https://www.cdc.gov/shigella) ይጎብኙ።

**ARLINGTON VIRGINIA**
Public Health
2100 Washington Boulevard
Arlington, VA 22204
ወደዚህ ቁጥር ይደውሉ 703-228-5200፣ አማራጭ #1፣ እና የእለቱን ነርስ ይጠይቁ
www.arlingtonva.us

ከቨርጂኒያ ጤና መምሪያ Shigellosis ኤፒዴሚዮሎጂ የመረጃ ቅጽ ተሻሽሎ የተወሰደ (መስከረም 2018)
https://www.vdh.virginia.gov/epidemiology/epidemiology-fact-sheets/shigellosis